የምርጫ ነክ ጉዳዮች ውሳኔ አጻጻፍ

ዳኞች ውሳኔዎችን በመጻፍ ልምድ ያላቸው ቢሆንም በምርጫ ጉዳዮች ላይ ውሳኔዎች በጣም በፍጥነት መጻፍ አለባቸው። ውሳኔዎቹ ወዲያውኑ ለመፈጸም በሚያስችል ሁኔታ ግልጽ መሆን አለባቸው። (የምርጫ ጉዳዮች በፍርድ ቤት የሚስተናገዱበት ሥነ ሥርዓት ረቂቅ ድንብ አንቀጽ 43)

ውይይት፡ ዳኞች የተለመደውን የውሳኔ አጻጻፍ ዘይ ከህጉ የጊዜ ገደብ ጋር እንዲስማማ በሚያደርግ መልኩ መቅረጽ ይኖርባቸው ይሆን?

ከዚህ በታች የተመለከተው ግልጽ እና አጭር የሆነ የውሳኔ ለመጻፍ የሚረዳ ዝርዝር (checklist) ነው።

የመግቢያ መረጃዎች-

- ሥልጣን
- የመዝገብ ቁጥር፣
- በጉዳዩ ላይ ተከራካሪ የሆኑ ሰዎች ስም፣ ቅሬታ አቅራቢ/ዎች እና መልስ ሰጪ/ዎች እና በጉዳዩ የሚያገባቸው ወገኖች
- የውሳኔው ቀን

አጭር ትንታኔ፡-

- አከራካሪው ጉዳይ በአጭሩ እና እየታየ ያለውን ክርክር ወይም ክስ
- ጭብጡን የሚያመለክተው ሀሳብ ሊወሰን የሚገባውን ጭብጥ በሚገባ የሚያሳይ። በውሳኔው የመጀመሪያው ክፍል ሊቀርብ ይገባዋል።

ማስረጃ እና ፍሬ ነገር

- በቅሬታ አቅራቢው, በመልስ ሰጪው ወይም በማንኛውም በሚያገባው ወገን የቀረቡትን ማስረጃዎች መጥቀስ ለምሳሌ የምስክሮች ምስክርነት፣ ፎቶግራፎች ፣ የውጤት መግለጫ ቅጾች
- በምርጫ ቦርድ የተሰበሰቡ ወይም የተጣሩ ማስረጃዎችን እንደ የምርጫ አስፈጻሚዎች ወይም የምስክሮች ቃል መጠይቅ መጥቀስ
- ክስ ከተሰማ መከራከሪያዎችን እና የቀረቡ ማስረጃዎች ካሉ በአጭሩ ማስቀመጥ
- ማስረጃዎችንም ትርጉም ባለው መንገድ አደራጅቶ ማስፈር ያስፈልጋል። ሁሉንም ማስረጃዎቹን በዝርዝር ማስቀመጥ ላያስፈልግ ይችላል። ለፍሬ ነገሩ ጭብጥ አስፈላጊ የሆነውን ማስረጃ በጣም በአጭሩ ማስቀመጥ ያስፈልጋል።
- የማያከራክር ማስረጃ እንደ አንድ ፍሬ ነገር ሊጠቀስ ይችላል። በአንድ አግባብነት ባለው የፍሬ ነገር ጭብጥ ላይ የቀረበ ማስረጃ ካከራከረ እውነታውን ማጣራት ያስፈልጋል።

ውሳኔ እና መፍትሔዎች

- ለፍሬ ጉዳዩ አግባብነት ያለውን ህግ መጠቀም
- ለፍርዱ ምክንያቶችን በግልጽ ማስቀመጥ
- የሚፈጸመውን ትዕዛዝ እና በማን እንደሚፈጸም በግልጽ ማስቀመጥ እና እንደአግባብነቱ ትዕዘዙ የሚፈጸምበትን የጊዜ ገድብ ማስቀመጥ